# አንተና እኔ (ከያሬድ ተሾመ ኖርዌይ)

እስካሁን አለህ ይለናለ እንዴ ...?
ደም ሊደባልቅ ሊበላ፤
በክፉ ዓላማዬን ልያሰላ፤
’ሄድ መስሎት ወደ ሌላ፤
ወደለመደበቱ ሸንገላ።

እርሱ ...! እንደ ቆላ ከብት በዉኃ ላይ ሊሰፍ፣
እጁን ስቶ ሊንከረፈፍ፣
ወጀቡ ወደገፋው ሊደገፍ፣
መርገጥ አቅቶት ሊዝለፈለፍ፣
በውኃ ትፋት ሊጠረነፍ፣

ታዲያ ’ኔን ...! ዓመትህ በዛ ይለኛል እንዴ...?
ይዘልቃል እንጅ ’ድነበረው፣
እንግዲያማ ዕውነት ምን ’ድሜ አለው።
ይልቅ አንተ ነህ ተላላው፣
ዓባይ ከፍታ የወደድከው፣
ኢሕአፓ ’ደሁ ሁሌም ያው ነው።

አትጠይቅም እንዴ መሠረቴን!
ያቋቋም ዓላማ ፅናቴን፣
ገድል ማኅደር መዛግብቴን፣
ያገር ፍቅር አንድነቴን፣
ኢትዮጵያዊ ደም ቀለሜን።

ታዲያ ’ኔን ... ዘገየህ ይለኛል እንዴ ይሄ ጅል!
... ከሌባ መንግሥት ቢዘል፣
... ዛሬም ከነገሰበቱ ቢዋዋል፣
... ሰብ ሕሊናውን ሽጦ ቢውል፣
... ጭንቅላቱ ቢያደርገው ቅል ... ።

ታዲያ ’ዳንተ ዕውነት ልተው ደ ’ጅብ ልሂድ፣
ወይስ ... ሆዴን ልብላው ራሴን ልውደድ፣
ልከድመው ’ዛው ላሽርግድ፣
እያወኩት ለሱው ልስገድ፣

ከርስ ላርገው ፅኑ ’ምነቴን፣
በርሱ መጀን ልመጃጀን፣
ወይስ ... እንደ ክረምት አጥቢ ልሁን፣
በአንድ ወቅት ’ድሜ ልበተን ...።

እንደ ውሻ ወደ ትፋቴ ልመለስ፣
እንደ ሸንኅፈት ዘራፊ ላጎንብስ፣
ወይስ እንደ ወንፊት የቀዳሁትን ላፍስስ።

አልገባህም እንዴ መዘግየቴ ኩልል ማለቴ መሆኑን!
የወርቅነቴ መገለጫ ያላማ ፅናቴ ዘመን፣
አንተና ’ኔን የሚለየን፣
የከፈልኩት ዋጋ ተመን፣
የ ዕምነቴ ስሌት ሚዛን፣
አገናዩ ደም መሆኑን !

EthioLion.Com

ድሮስ ምኑን አውቀኸው ...
...የህላዌውን ምስጢር፤
ያንዱ መሄድ ላንዱ መኖር።
እየሞቱ ያልሞቱትን ...
የልቤን ገድሎች ብቆጥር
ሞረሽ! የትግል ጀግኖቼን ብዘክር፣
ያንድ መዝሙራቸዉን ብዘምር፣
እነሱን አወድሼ ብቀር፣
ሞታቸው ከብራቸው ለነበር፣
እልፍ ዓመታትን ብቆጥር፣
የት ይገባሀል ይህ ክብር ... ።

አለህ ...? ይለኛል እንዴ ይህ ድንብር!

ዕውነት ምን መኖር አለው፣
ይኖራል እንጅ ’ደ ነበረው፣
ለባለ ልብ አገር ላለው፣
ድሮም ’ማቀው ኢሕአፓን ነው።
አታነብም እንዴ መሠረቴን፣
ያቋቋም ዓላማ ፅናቴን፣
ገድል ማጎደር መዛግብቴን፣
ያገር ፍቅር አንድነቴን፣
ኢትዮጵያዊ ደም ቀለሜን።

አጥፋ ...! ይለኛል እንዴ የኔን ቀንዲል፣
ከሌባ መንግሥት ዳግም ቢዘል፣
ዛሬም ከነገሰበቱ ቢዋዋል፣
ይጨልም መሰለው እንዴ በንፋስ፣
ብጉራ ጠናኝ በሜዳ ክስ፣
በሸንገላህ ባንተ ምላስ።

አልገባህም እንዴ! የኔ ቀንዲል ...
ወደነፈሰበቱ ’ምይወግን።
በልቤ ውስጥ የበራ መሆኑን።
ከትግሌ ጋር መለኮሱን።
ባደረ ቁጥር መድመቁን።

ለነገሩ ምኑን አውቅኸው ...
የዓላማ መቅረዙን ህብር፣
እንዴት እንደበራ ’ሚቀር፣
የህላዊውን ምስጢር፣

ሞረሽ! ... የበኩር ጀግኖቼን ብዘክር፣
የፋና ወጊዎቼን መዝሙር፣
እነሱን አወድሼ ብቀር፣
ስላሳ ስድስት ዓመታትን ብቆጥር፣
... የት ይገባሀል ይህ ክብር!!

EthioLion.Com

EthioLion.Com